# ለወሬ ነጋሪው

(ከኃይሉ በለሳ)

ይቻል ነበር እኮ በሃቅ መተቸት

ለወሬ ለዝና ለታሪክ መመቸት

መካድ ግን ፀያፍ ነው ያልሆነ ስም መስጠት።

ካስፈለገ ደግሞ በታሪክ መነገድ

ቀጥታ መወገን ባለጊዜ መውደድ

ደግሞ ምን አመጣው በሞት መቀለድ

በመኢሶን ቆዳ ተሽፋፍኖ መሄድ።

ይሻል ነበር እኮ ባገር ቋንቋ መፃፍ

ደረት የሚያስነፋው በህዝብ እንዲደገፍ

አንገት የሚያስደፋው በወጉ እንዲነቀፍ

ምስክር የሚሻው በአዋጅ እንዲለፈፍ

ቅጣት የሚገባው በአበው እንዲገረፍ

ሽልማት የሚወስድ በተራ እንዲሰለፍ።

ግን ማንን አስደሰትክ? ቋንቋ ስትቀይር

የሰራኸው ታሪክ በአማርኛ ነበር።

እናትህ አባትህ ወገንህ በሙሉ

አንተን ያስተማሩት እነሱ ሳይበሉ

እህትህ ወንድምህ ጓደኞችህ ሁሉ

ይኸ ሰው አበደ? ምን ነከቶታል? አሉ።

ባዲሱ ጥበብህ በፈረንጅ የለፋህ

የአንገትህ ላይ ክታብ አማርኛው ጠፋህ?

ወይ እንደታሪክህ በቋንቋም ተከፋህ።

አለያስ ለመደበቅ ከሰው ለመሸሽግ

ከባንዳ መኢሶን ስትወግን ከደርግ።

ከዚያች ቀይ መፃህፍ የማኦን ጠቃቅሰህ

በላኢላ ካህሊድ ጀብዱ ራስክን ዳብሰህ

በነአደፍርስ ብዕር ኃይሌን አረካክሰህ

ከአርባ ዓመት በኋላ ቅርሻትክን ላልሰህ

መፃፊያ ብዕርክን ቀለሙን አፍሰህ

ፈሪ ነበርን አልከን "ጀግንነት" ተውሰህ።

እሳቱን ጨብጦ አመዱን የፈራ

በድቅድቅ ጨለማ ችቦውን ያበራ

ከአፋፍ ላይ ሆኖ ጎህ ሲቀድ ያወራ

ከታንክ አፈሙዝ ስር አመፅን የጠራ

ደም እየዘነበ ህይወትን የዘራ

ከሰፊው ህዝብ ጋር ታሪክን የሰራ

ማን ቀባጥር አለው ? ማን አለው ስም ጥራ ?

ማንን ድሮ ይሆን ለጥፋት ሙሽራ ?

ምንድን ተሸለመ ማን ሰጠው አደራ ?

አሜሪካ ገብቶ ከፍራት ጎተራ
ራሱን ገረፈ በክህደት ከዘራ።
በደስታ ተጠምዶ ሲፈታ የሮጠ
በጦር ሜዳ ውሎው ማርኮ ያመለጠ
እውነት ከመመስከር ፍራትን መረጠ
ጎርሶ ሲዘላብድ ምላሱን ቆረጠ
ባረቄና በጫት ክብሩን ዛሬ ዋጠ።
ከፊዳ አደፍርስን መርጦ የደገፈ
ጥፋትን የጠላ በጎህ የለፈፈ
ማን ቀማው አገሩን ?
ማን ቀማው ቋንቋውን?
ማን ነጠቀው ሚስቱን ?
በምን አኮረፈ ?
የርሱን ታሪክ ሽጦ የሰው ወሬ ፃፈ።
በድኔን ድፈር እንጅ እኔን አትነካም
ሱሪ ልበስ እንጅ በወንድ አትለካም
መትረየስ ያዝ እንጅ ጀግና መች ሆንክና
አንተን የወለደች እናት ትቅር መክና።
ፈቅጀ ከምሰጥ አንተን ለመሰለ
የእናቱን ጡት ቆራጭ ህፃን ለገድለ
በክብር እመርጣለሁ የእናቶቾን እጣ

የእህቶቸን እጣ

ቀይ ደም አይደለም ወይ ከእኔ የሚወጣ ?

አንት ልክስክስ ባንዳ የፋሽስት ቡችላ

እኔን ግደልና እሱን ቆርጠህ ብላ።

ብላ ስትተፋበት

በክብር ስትሞት

እናቸንፋለን እንዳለች ስትቀር

ትዕዝ አይልህም ወይ ይህን ስትናገር ?

ጀሮህ ተውትፎ መልካም እንዳይሰማ

ዐይንህ ስቡ ጋርዶት ካንተ እንዳይስማማ

አፍህ ብር ሞልቶት እውነት ከመመስከር

ይሁን በመረጥከው በውሸትህ ስከር

ተጓዝ በሚቀናህ በፍራትህ ዕፈር።

እየቀጠቀጡት አንተን ሳያጋልጥ

እየተታኮሰ ሩጠህ ስታመልጥ

ሞት ለፋሽስት ብሎ መፈክር ያሰማ

ግብ ግብ ገጥሞ መሳሪያ የቀማ

እያውለበለበ የኢህአፓን አርማ

ሚስጥሩን ጠብቆ ህይወቱን የዋጣት

አርያው ጓደኛህ ያለፈው በኩራት

እራስክን እንድታይ ቀድሞ የወደቀ

በጎህ እንድታብብ ድፍረት የመረቀ

እንዲህ ያረገውን ጓድህን እረሳህ ?

ወይስ በድነህ ነው ሙተህ የተነሳህ ?

ምንድን ነው ዳርዳርታው ምንድን ነው ሃፍረቱ ?

አንተ የቁም እንቅልፍ አንተ የሰው ከንቱ።

ታምሜ ነው በለን ስክሬ ደንዝዤ

አፈ ታሪክ የፃፍኩ እውነቱን ሰርዤ።

አታውቃቸው እንደሁ ላስተዋውቅህ ዛሬ

አገራቸው ሩቅ ስማቸው አጅሬ

ማተባቸው ወፍራም ከዳት የመያውቁ

ማደርን የጠሉ ህይወትን የናቁ

እጅ ላለመስጠት ከፎቅ የወደቁ

በዕልልታ ዝማሬ ሞትን ያቸነፉ ስቅይን ያጠቁ።

በዘር በሃይማኖት በፆታ ሳይምሉ

ትልቋ ኢትዮጵያ ነፃ ትሁን ያሉ።

ከምስራቅ ከምዕራብ ከደቡብ ከሰሜን

ከከተማ ገጠር ፍትህ ርዕትህን ሰላምን አስበን

ሊገሉን ሲመጡ እኛም ቃታ ስበን

ባንዳን አንበርክከን መቃብር አስመን

ፋሽስት አንቀጥቅጠን

ዓለምን አናውጠን

ጥቁር ቦልሸቪኮች ከነጮቹ በልጠን

ዛሬን አይሁንና በሁሉ ተመርጠን

ይህ ነው ኢህአወሊ ባዋጅ የሰደብከው

ይኸ ነው ኢ ህ አ ፓ በስሙ ያፈርከው

ይኸ ነው ኢ ህ አ ሠ ፈርተህ ያዋረድከው

ያንተን ታሪክ ሽጠህ ወሬ ለንገርከው

በርከክ በልና ይቅርታ ጠይቀው።

ህዳር 2006 ዓ. ም.